Hamlin Fistula Ethiopia

# ሐምሊን ዜና መጽሔት

ቁጥር 2 ፤ ሐምሌ 2009 ዓ.ም.

በሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ በየሦስት ወሩ እየተዘጋጀ ለሠራተኞቹ የሚሰራጭ




## በውስጥ ገፆች

- የሐምሊን ሚድዋይፎች ምረቃ 2
- ዓለም አቀፍ ፓርትነርስ ስብሰባ 4
- የቀዶ ጥገና መብራቶች ከአንቶይን ቤተሰብ 5
- የቻቻ ቡድን ድጋፍ 7
- የፊስቱላ ጉዳት ማስወገጃ ቀን 9
  - በአዲስ አበባ ፊስቱላ ሆስፒታል 9
  - በመቀሌ ሐምሊን ፊስቱላ ማዕከል 10
- ቀሪ ዘመንሽ የተባረከ ይሁን 13
- የሐምሊን ምልክቶች 14

## 7ተኛው ዙር የሐምሊን ሚድዋይፎች ተመረቁ

*ተመራቂ ሚድዋይፎቼ፣ በአራት አመት የሐምሊን ቆይታችሁ የተማራችሁት ዋናው ነጥብ ፍቅርን እንደሆነ አምናለሁ፡፡ ስራችሁን ስታፈቅሩ መላ ቀልባችሁን እሱ ላይ ታደርጋላችሁ፡፡ ይህን ጊዜ ስራችሁ የምትዝናኑበት ይሆናል እንጂ አያሰለቻችሁም፡፡ ስራው ደግሞ አዲስ ጨቅላን ወደ ምድር ማምጣት ሲሆን ከሁሉም በላይ ያስደስታል፡፡ ዘመኔን ሙሉ ከቀድሞ ባለቤቴ ጋር ስተጋለት የኖርኩት የወሊድ ፊስቱላን ከዚች አገር የማጥፋት ህልሜን የምታሳኩት እናንተ ናችሁ፡፡ ለእንደኔ አይነቱ የ93 ዓመት አዛውንት ይህ ሲሳካ ማየት የማይቻል ይሆናል፡፡ በእናንተ ዘመን እንደምታሳኩት ግን አልጠራጠርም፡፡*

ዶ/ር ካትሪን ሐምሊን
በምረቃ ስነ-ስርዓት ላይ ከተናገሩት



ሚድዋይፎችን ሐምሌ 8፣ 2009 ዓ.ም በኮሌጁ ቅጥር በደማቅ ስነ-ስርዓት አስመርቋል፡፡ በስነ-ስርዓቱ ላይ የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ተባባሪ መስራች ዶ/ር ካትሪን ሐምሊንን ጨምሮ በባህርማዶ የድርጅቱ ለጋሽ ተቋማት ተወካዮች፣ የድርጅቱ የበላይ ጠባቂዎች፣ የቆንፅላ

ከተመሠረተበት 1999 ዓ.ም ጀምሮ የሐምሊን ሚድዋይፈሪ ኮሌጅ ከክፍለሃገር 2ተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚመለምላቸውን ጎበዝ ሴት ተማሪዎችን በኮሌጁ ተቀብሎ ለአራት አመታት በሚድዋይፈሪ የመጀመሪያ ዲግሪ በነፃ አሰልጥኖ ወደየመጡበት አካባቢ ባሉ የመንግስት ጤና ጣቢዎች ላይ መድቦ እያሰራ ይገኛል፡፡ ዘንድሮም ለ7ተኛ ጊዜ ያሰለጠናቸውንና በሙያ ክህሎታቸው የላቁ 20 ሴት

ተወካዮች፣ የመንግስት ባለድርሻ አካላት፣ ከክልል የሐምሊን ማዕከላት ተወካዮችን ጨምሮ ከዚሁ ከአዲስ አበባ የሐምሊን የስራ ክፍሎች የተወከሉ ሰራተኞች እና የበላይ ኃላፊዎች እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው የተመራቂ ቤተሰቦች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ዋና ስራ አስፈፃሚ ዶ/ር ተስፋዬ ያዕቆብ በመክፈቻ ንግግራቸው ተመራቂዎቹን

እንኳን ደስ አላችሁ በማለት አሁን እናንተ የሐምሊን አምባሳደሮች ናችሁ፤ እንደቀደሙት ተመራቂዎቻችን ሁሉ በየተመደባችሁበት ጤና ጣቢያ ጥራት ያለው አገልግሎት በመስጠት አምባሳደርነታችሁን እንደምታረጋግጡ እምነቴ ነው ብለዋል፡፡



ባጠቃላይ ውጤቷ የዚህን አመት 20 ተመራቂዎች በመምራት የበላይ ሆና ያጠናቀቀችውና የሐምሊን ሜዳሊያዋን በዶ/ር ሐምሊን እጅ ያጠለቀችው ተመራቂ ሃብታም ሙሉጌታ ሆናለች፡፡ ይህን ድል ከአመታት በፊት በኮሌጁ ተማሪዎችና ሰራተኞች ላይ ጉዳትን ካስከተለው የመኪና አደጋ ተርፋ ለአንድ አመት ትምህርቷን እንድታቋርጥ ከተገደደች በኃላ ያገኘችው መሆኑ ድሉን ልዩ ያደርገዋል፡፡

የዘንድሮ ተመራቂዎችን ጨምሮ እስከአሁን ከኮሌጁ 125 በሙያ ክህሎታቸው የላቁ ሚድዋይፎች የተመረቁ ሲሆን የሐምሊን ሚድዋይፎች ተመድበውባቸው የእናቶች ጤና አገልግሎታቸው በሐምሊን የሚታገዝ የመንግስት ጤና ጣቢያዎች ቁጥርም በመላ ሃገሪቱ 36 ደርሷል፡፡

## ዜና ዕረፍት

እኛ የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ሠራተኞች በእህታችን ግስታኔ በላይነህ ህልፈተ ህይወት የተሰማንን ጥልቅ ሀዘን መግለጽ እንፈልጋለን፡፡ እህታችን ግስታኔ በሐምሊን ፊስቱላ ይርጋለም ሴንተር ከስምንት ዓመታት በላይ በትጋትና በቅንነት ስታገለግል ቆይታ ሐምሌ 23፣ 2009 ዓ.ም. ባደረባት ህመም ምክንያት ከዚህ ዓለም ተሰናብታለች፡፡

በዚህ መሪር የሀዘን ወቅት ለቤተሰቦቿና ለወዳጅ ዘመዶቿ በሙሉ መጽናናቱን እየተመኘን እግዚአብሔር ነብሷን በገነት ያኑሪልን ዘንድ እንጸልያለን፡፡



## የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ፓርትነርስ ስብሰባ ተካሄደ



የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ፓርትነርስ ስብሰባ (Hamlin Fistula Ethiopia International Partners Meeting) ግንቦት 25 እና 26፣ 2009 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ፊስቱላ ሆስፒታል ግቢ ውስጥ ተካሄደ፡፡ በስብሰባውም የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ትረስቲዎችና የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ የቦርድና የማናጅመንት አባላት ተገኝተዋል፡፡

ለሁለት ቀናት በቆየው በዚህ ስብሰባ ላይ በድርጅቱ አዲስ ስትራቴጂክ እቅድ ላይ ሰፊ ገላጻና ውይይት ተካሂዷል፡፡በተጨማሪም በድርጅቱ ፕሮግራም ዘርፎች የዩሮጋይኒኮሎጂ ስልጠናን ጨምሮ የዓመቱ ክንውንና የቀጣይ ዓመት ዕቅድ ላይ ውይይቶች ተደርገዋል፡፡ አጠቃላይ የድርጅቱ ክንውንና የበጀት ሪፖርትም ለውይይት ቀርቧል፡፡

የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ፓርትነርስ ስብሰባ በየዓመቱ የሚካሄድ ሲሆን ዓላማውም የድርጅቱን ዓመታዊ ክንውን ከመገምገም ባሻገር የቀጣይ ዓመት ዕቅድና በጀት ላይ በመወያየት የጋራ ግንዛቤ ለመያዝ ጭምር ነው፡፡



# የአንቶይን ቤተሰብ አዳዲስ የቀዶ ጥገና መብራቶች ለሐምሊን

## “ደማቅ ብርሃን ለሐምሊን ፊስቱላ ሆስፒታል ድንቅ ስራ ቀጣይነት ለአንቶይን ቫንደን ዌልደንበርግ መታሰቢያነት ከቤተሰቡ በፍቅር የተበረከተ”

አቶ አንቶይን፣ ባለቤቱ ዋይስ እና ቤተሰባቸው የሐምሊንን ህይወት አድን ስራ ለመጀመሪያ ጊዜ የተረዱት መስራቿ ዶ/ር ካትሪን ሐምሊን ከዓመታት በፊት ለስራ ጉብኝት ወደ ሃገራቸው ሆላንድ ሄደው በአካል ከተዋወቁና ካወሩ በኃላ ነው። ከዚያን ጊዜ አንስቶ ሰዓሊው አንቶይን እና ባለቤቱ ዋይስ ከሐምሊን ጋር ያላቸው ቁርኝት ጠንክሮ ሆላንድ ከሚገኘው የኛ አጋር ድርጅት ጋር በመሆን ስራውን ሲያግዙ ቆይተዋል።



በ2006 ዓ.ም አቶ አንቶይን ባደረበት ህመም ከዚህ አለም ሲያልፍ በተወው የኑዛዜ ቃሉ በህይወት ሳለ የሳላቸው ድንቅ ስዕሎቹ ተሽጠው የሚገኘው ገቢ የሐምሊንን ስራ ለማገዝ እንዲውልለት በማሳሰብ ቤተሰቡ ለሐምሊን ስራ ያለውን ጥልቅ መቆርቆር በደስታ ብቻ ሳይሆን በመጨረሻዋ የምድር ቆይታ ወቅትም አሳይቷል። ይህንንም ኑዛዜ ለማስፈፀም ባለቤቱ ዋይስ ከዶ/ር ካትሪን የረጅም ጊዜ ቅርብ ወዳጅ እና የሆላንድ አጋር ድርጅታችን አባል ዶ/ር ባርባራ ጋር በመሆን ሲሰሩ ቆይተዋል።

በቅርቡ ታዲያ የአንቶይን ስዕሎች ተሽጠው በተገኘው ገቢ አስቀድሞ በህክምና ቡድናችን በተለየ ፍላጎት መሰረት ባለቤቱ ዋይስ እና ዶ/ር ባርባራ ሁለት አዳዲስና ዘመናዊ የቀዶጥገና መብራቶችን ከሆላንድ ገዝተው እዚህ ሆስፒታላችን ድረስ በመገኘት አስረክበዋል። በሰኔ 16 2009 ዓ.ም ከሰዓት በኃላ በቀዶ ጥገና ክፍል በተከናወነው የርክክብ ስነስርዓት

ዶክተር ካትሪን፣ዶክተር ፊቃደና ሌሎች የህክምና ቡድናችን አባላት ተገኝተው የአንቶይን ቤተሰብ በተለይ ባለቤቱ ዋይስን እንዲሁም ዶክተር ባርባራን አመስግነው መብራቶቹን ተረክበዋል፡፡

የሐምሊን ህክምና ቡድን መሪ የሆኑት ዶክተር ፊቃደ ባደረጉት የምስጋና ንግግራቸው የቀዶ ጥገና መብራቶቹ በቅርቡ ድርጅቱ ከሌሎች አጋሮች ጋር ሐምሊን አገልግሎቶቹን በእጅጉ ለሚፈልጉት ለእነዚህ ምስኪን የፊስቱላ ተጎጂዎች ሳያቋርጥ እየሰጠ መቀጠል የቻለው እንደ አንቶይን ያሉ ደግ ግለሰቦች በሚያደርጉት ድጋፍ ነው ያሉት ደግሞ መስራቿ ዶ/ር ካትሪን ናቸው፡፡ ለሚቹ አንቶይንም ፈጣሪ ነፍሱን በገነት ያኖራት ዘንድ ዶ/ር ካትሪን ተመኝተዋል፡፡



እነዚህ እያንዳንዳቸው ወደ አራት መቶ ሺህ ብር ገደማ ወጪ የተደረገባቸው የቀዶጥገና መብራቶች እላያቸው ላይ እንዲህ የሚል መልክት ይነበባል፡

“ደማቅ ብርሃን ለሐምሊን ፊስቱላ ሆስፒታል ድንቅ ስራ ቀጣይነት
ለአንቶይን ቫንደን ዌልደንበርግ መታሰቢያነት ከቤተሰቡ በፍቅር የተበረከተ”

ለጀመረው የዩሮጋይኒኮሎጂ ስፔሻሊቲ ስልጠና የሚኖራቸው አስተዋፅዖ ጉልህ መሆኑን ጠቅሰው ሐምሊን የሚታወቅበትን ጥራት ያለው አስተማማኝ ህክምና መስጠቱን አጠናክሮ እንዲቀጥል የአንቶይን ቤተሰብ ላበረከተው ትልቅ ስጦታ በታካሚዎቻችን ስም አመሰግናለው ብለዋል፡፡



# ለሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ድጋፍ ለማሰባሰብ 69 ኪ/ሜ ርዝመት ያለውን የጄኔቫ ሐይቅ በዋና ያቋረጠው የቻቻ ቡድን







ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ላለፉት ከአርባ በላይ ዓመታት በወሊድ ፊስቱላ ሳቢያ ስነልቦናዊና ማህበራዊ ቀውስ ለደረሰባቸው ምስኪን የገጠር ሴቶች ነፃ ህክምና እየሰጠ ያለው ሙሉ በሙሉ ከለጋሾች በሚያገኘው የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ ነው፡፡ በመላው አለም ለተቋሙ የገቢ ማሰባሰብ ስራን ከሚሰሩት ድርጅቶች በተጨማሪ ግለሰቦች በቡድንም ሆነ በተናጠል በራስ ተነሳሽነት የሚያደርጉት እገዛ ድርሻው ትልቅ ነው፡፡ ስራችንን ካዩ በኃላ ወደየሃገራቸው ሲመለሱ ገቢ ለማሰባሰብ አንዳንዶች በባዶእግር ይሮጣሉ፤ ሌሎች በበረዶ ላይ ይንዛሉ፤ ቀሪዎች ደግሞ ውቂያኖስ ተሻግረው በጀብድ የተሞላ ጉዞን ያደርጋሉ፡፡ ሁሉም ግን አላማቸው አንድና ያው ነው፡፡ በሃገራችን የገጠር ሴቶች ላይ በወሊድ ሳቢያ የሚደርስ የፊስቱላን ጉዳት ማቆም፡፡

የዛሬ ሁለት አመት ገደማ ነው የአዲስ አበባ ፊስቱላ ሆስፒታልን የማየት እድል ያገኘሁት ትላለች የ17 ዓመቷ ወጣት ስዊዘርላንዳዊት ተዶሽያ ካትስያፕስ፡፡ በወቅቱ በእኔ እድሜ ያሉ ምስኪን ሴቶች ስለመኖሩ እንኳን በማላቀው የወሊድ ፊስቱላ ጉዳት ሰበብ ከባድ ስነልቦናዊና አካላዊ ጉዳት ደርሶባቸው ሳይ ከልቤ አዘንኩኝ፤ በተቻለኝ ሁሉ እነሱን ለማገዝ ለራሴ ቃል ገባሁኝ፡፡

በዚህ መነሻነት ተዶሽያ ወደ አገሯ ከተመለሰች በኃላ ስላየችው አሳዛኝ ክስተት ለጓደኞቿ በመንገር እንዲያግዟት ማሳመን ቻለች፡፡ ለገንዘብ ማሰባሰቢያነት የመረጡት ሁነትም ቀዝቃዛውን የጄኔቫ ሐይቅን በዋና የማቋረጥ ሆነ፡፡ ራሳቸውን የቻቻ ቡድን ብለው የሰየሙ እንደሷ በአስራዎቹ ዕድሜ ክልል ያሉ ስምንት ልጃገረዶች ለዚህ ፈታኝ ተግባር ራሳቸውን

ማዘጋጀት ጀመሩ፡፡ በጣም ቀዝቃዛ፣ በአደገኛ የባህር ፍጡራን በተሞላ ወደ 69 ኪ.ሜ ርዝመት ያለው ሐይቅን በዋና ለማቋረጥ ማሰብ የዕብደት ተግባር ይመስላል፤ ለቻቻ ቡድን ግን ለእህቶቻቸው የሚከፈል ጥቂት መስዋዕትነት ሆነ፡፡ አላማቸውን የሰሙ ግለሰቦችና ድርጅቶች ባደረጉት ድጋፍ 76ሺህ ዶላር በማሰባሰብ የቻቻ ቡድን የጄኔቫ ሃይቅን ለ24 ሰዓታት ዋኝተው በድል ተወጡት፡፡

ሐምሌ 5፣ ሐሙስ ከሰዓት፣ በዋናው ሆስፒታል ግቢ በተከናወነ ስነስርዓት ተዶሽያ የቻቻ ቡድንን ወክላ፣ ከስዊዝ ደጋፊ ድርጅት ሊዛ ጋር በመሆን፣ ቡድኑ ያሰባሰበውን የገንዘብ ድጋፍ ለዶ/ር ካትሪን አስረክባለች፡፡ በዝግጅቱ ላይ ተዶሽያ ስትናገር ጥቂት እንደዋኘሁ የውሃው ቅዝቃዜ እንባዬ እስኪመጣ ተሰምቶኝ ነበር፤ ወዲያው ግን እነዚያን የኔ እኩያ የፊስቱላ ተጎጂዎችን ህመም ሳስታውስ የኔ በጣም ትንሹ እንደሆነ ለራሴ ነግሬ ማሳካት ችያለው፤በዚህም በጣም ደስተኛ ነኝ ብላለች፡፡

ዶ/ር ካትሪን በበኩላቸው ልጅ ሆነሽ እንደአዋቂ በማሰብ እነኚህ የኛን ድጋፍ በእጅጉ የሚፈልጉ ምስኪን ሴቶችን በማገዝሽ በጣም አመሰግናለሁ ብለዋታል፡፡



# ዓለም አቀፍ የፊስቱላ ጉዳት ማስወገጃ ቀን በአገር አቀፍ ደረጃ በአዲስ አበባ ፊስቱላ ሆስፒታል ተከበረ

ዓለም አቀፍ የፊስቱላ ጉዳት ማስወገጃ ቀን እ.አ.አ. ግንቦት 23፣ 2017 በአገር አቀፍ ደረጃ በአዲስ አበባ ፊስቱላ ሆስፒታል "ተስፋ፣ መዳንና ክብር ለሁሉም" በሚል መሪ ሀሳብ ተከበረ። በክብረ-በዓሉም ዶ/ር ካትርን ሐምሊንና የፊስቱላ ታካሚዎችን ጨምሮ ከፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከተባበሩት መንግስታት የስነ-ህዝብ የገንዘብ ድጋፍ፣ከፓዝ ፋይንደር ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ፣ ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ፣ ከጅማ ዩኒቨርሲቲ፣ ከኢትዮጵያ ሚድዋይፎች ማህበር፤ ከኢትዮጵያ ጤና አጠባበቅ ማህበር፣ ከኦሮሚያ ጤና ቢሮ እና ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተወከሉ ባለሙያዎች ተገኝተዋል።



የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ዋና ስራ አስፈፃሚ፣ ዶ/ር ተስፋዬ ያዕቆብ፣ በመክፈቻ ንግግራቸው ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ የዚህ ክብረ-በዓል ተሳታፊ እና የመሪ ሀሳቡ ተካፋይ በመሆኑ ደስታቸውን ገልጸው፣ ቀኑን ለማክበር የአዲስ አበባ ፊስቱላ ሆስፒታል ትክክለኛ ቦታ እንደሆነ ተናግረዋል። በተጨማሪም ለዶ/ር ካትርን ሐምሊንና በህይወት ለሌሉት ባለቤታቸው ዶ/ር ሬጅናልድ ሐምሊን ምስጋናቸውን አቅርበዋል። "ከማንም በላይ ባለውለታችን ናቸው። ላለፉት 50 ዓመታት እነሱ ያቋቋሙት ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ከ50, 000 በላይ የፊስቱላ ተጎጂዎችን በማከምና መልሶ በማቋቋም ትልቅ አገራዊ ስራ ሰርቷል። እንደ አገር ልንኮራባቸው ይገባናል፤ ምስጋናችንም ይድረሳቸው፣" ብለዋል።

የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ወክለው የተገኙ የተከበሩ ዶ/ር እሸቱ ከበደ ባደረጉት ንግግር የዕለቱ መከበር በአለም ላይ ስለ ፊስቱላና እያስከተለ ስላለው ጉዳት ግንዛቤ ከማስጨበጥ ባሻገር ፊስቱላን ለማጥፋት እየተደረገ ላለው ዘመቻ ተጨማሪ የፖለቲካና የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ትልቅ መድረክ ይፈጥራል ብለዋል።

በዕለቱ በተካሄደው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ዶ/ር ፈቃደ አየናቸው እንደተናገሩት በተራዘመ ምጥ ምክንያት የሚፈጠረው የፊስቱላ ጉዳት በዓለማችን ላይ እየቀነሰ ቢመጣም በህክምና ስህተት እየተፈጠረ ያለው የፊስቱላ ጉዳት ዓይነት ግን ትኩረት እንደሚያስፈልገው ጠቁመዋል።

ዓለም አቀፍ የፊስቱላ ጉዳት ማስወገጃ ቀን በየዓመቱ እ.አ.አ. ግንቦት 23 በዓለም አቀፍ ደረጃ ይከበራል።

# የአለም ፌስቱላ ቀን በመቀሌ



ሜይ 23 አለም አቀፍ የወሊድ ፌስቱላን የማጥፋት ቀን በክልል ደረጃ በትግራይ ክልል መቀመጫ መቀሌ ላይ በመቀሌ ሐምሊን ፌስቱላ ማዕከል ቅጥር ግቢ ውስጥ በደማቅ ስነ-ስርዓት ተከብሯል፡፡ ልክ በፌደራል ደረጃ እንደነበረው ሁሉ የመቀሌው ክብረ-በዓልም በክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ በሚመራው የመቀሌ ሐምሊን ፌስቱላ ማዕከልን ጨምሮ በክልሉ የፌስቱላ መከላከል ግብረሃይል አባል ድርጅቶች አዘጋጅነት የተካሄደ መሆኑን ዶ/ር መላኩ ከመቀሌ ያደረሱን መረጃ ያስረዳል፡፡ በዝግጅቱ ላይ ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጡ 50 ያህል ተማሪዎች፣የክልሉ ፖሊስ ማርሽ አባላት፣ ሁለት ታዋቂ የትግርኛ ዘፈን አርቲስቶች(አወጣሽና አዚዝ) እንዲሁም በአጋጣሚ ሐምሊን በዩሮጋይኒኮሎጂ የስልጠና ፕሮግራሙ እያካሄደ ላለው የማህፀን መውጣት (ፕሮላፕስ)ህክምና ዘመቻው ከክልሉ ተመልምለው የመጡትን ጨምሮ ከሃምሳ በላይ ታካሚዎች፣ እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተሳትፈዋል፡፡

ክብረ-በዓሉ በሐምሊን ማዕከል መከበሩ የክልሉ መንግስት ለሐምሊን ፌስቱላ ኢትዮጵያና በአጠቃላይ ለወሊድ ፌስቱላ የሰጠውን ትኩረት የሚያሳይ እንደሆነ የጠቀሱት የመቀሌው ማዕከላችን ዋና ሃኪምና ሜዲካል ዳይሬክተር ዶ/ር

መላኩ አብርሃ፣ በክልል ደረጃ የተዋቀረው የፊስቱላ መከላከል ግብረሃይል ወደተጨባጭ ስራ በተደራጀ መልኩ እንዲገባ በማድረግ የዘርፉ የመንግስት ግብ እንዲሳካ የክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ እያደረገ ላለው አስተዋፅኦ ሊመሰገን ይገባል ብለዋል፡፡ ዶ/ር መላኩ አክለውም በክብረ-በዓሉ ላይ የወሊድ ፊስቱላን የመከላከል ጉዳይ ለሐምሊን የሚተው ተግባር ብቻ እንዳልሆነ፣ ይልቁንም መንግስትን ጨምሮ የሁሉንም ባለድርሻ አካላትን እንዲሁም የማህበረሰቡን የጋራ ርብርብ የሚጠይቅ እንደሆነ ለማስገንዘብ ተችሏል ብለዋል፡፡ በዕለቱ የክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ አሁን የተጀመረውን መነቃቃት አጠናክሮ ለመቀጠልና ፊስቱላ የአገሪቱ የጤና ችግር እንዳይሆን የማድረግ አገራዊ ግብ እንዲሳካ ከሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ጋር በጋራ ለመስራት ቃል መግባቱንም ዶ/ር መላኩ አስረድተዋል፡፡ ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ከአዘጋጆቹ አንዱ እንደመሆኑ መልዕክቶች ያረፉባቸው 200 ቲሸርቶችን አሳትሞ ለተሳታፊዎች አሰራጭቷል፡፡

ከዚሁ የጋለ የበዓል አከባበር ስሜት ጋር በተያያዘ የሐምሊን ህክምና ቡድን ሌላ አንድ የተሳካ ዘመቻ መቀሌ ላይ አካሂዷል፡፡ ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ በዘርፉ ያካበተውን የበርካታ አመታት ልምድ ተጠቅሞ የወሊድ ፊስቱላንና አጠቃላይ የወሊድ ወቅት ጉዳት ህክምናን አሁን ካለው በጥራትም በውጤታማነትም ለማሳደግ የተለያዩ እርምጃዎችን እየወሰደ ይገኛል፡፡ ከነዚህ እርምጃዎች መካከልም በስልጠናና ምርምር ዘርፍ ከሁለት አመታት በፊት ከመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ህክምና ክፍል እና ከቅዱስ ጳውሎስ የህክምና ትምህርት ቤትና ከዓለም አቀፍ የፊስቱላ ፈንድ ጋር በጋራ የዩሮጋይኒኮሎጂ ስፔሻሊቲ ስልጠናን መጀመሩ ይጠቀሳል፡፡ በዚሁ ፕሮግራም አማካኝነትም የወሊድ ፊስቱላን ያህል ስነልቦናዊና ማህበራዊ ጉዳትን በእናቶች ላይ የሚያደርሰውን


ተስፋን ፈዉስን ክብርን ንኹለን ተጠቃዕቲ ሕማም ፌስቱላ
ዓለም ለኸ መዓልቲ ምክልኻል ሕማም ፌስቱላ ጉንበት 16- 2009 ዓ/ም

ሌላኛው የወሊድ ጉዳት የማህፀን መውጣት ችግርን ባለው የካበተ ልምድ ውጤታማ የህክምና ዘመቻ በባህርዳርና ይርጋለም ማዕከላት በዚህ ዓመት ሰርቷል፡፡ እ.አ.አ ከሜይ 15-26፣2017 የዚሁ ፕሮግራም ቀጣይ ዘመቻ መቀሌ ሐምሊን ፊስቱላ ማዕከል ላይ በክልሉ ጤና ቢሮ ትብብር ለተለዩ 39 ተጎጂዎች የተሳካ ነፃ ህክምና ተሰጥቷል፡፡

በዘመቻው በዶ/ር ሬናቴ፣ የስልጠና ፕሮገራሙ ዳይሬክተር፣ የሚመራ 11 አባላት ያሉት የህክምና ቡድን የተሳተፈ ሲሆን ከተሳታፊዎቹ ሶስቱ አንጋፋ ሃኪሞች ከሐምሊን የተወከሉ ሰልጣኞች ናቸው፡፡ ዶ/ር መላኩ ፣የመቀሌ ማዕከል ኃላፊና በስልጠና ፕሮግራሙ የሁለተኛ አመት ሰልጣኝ፣ ዘመቻውን አስመልክቶ ባዘጋጁት የአፈፃፀም ሪፖርት ላይ እንዳስቀመጡት የክልሉ ጤና ቢሮ ታካሚዎቹን በመለየት፣ የመቀሌ ሆስፒታል ደግሞ እንደ አውቶክሌቭ ያሉ ቁሳቁሶችን ከባለሙያ ጋር ድጋፍ በማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ ተሳታፊ የአይደር ሆስፒታል የፅንስና ማህፀን ተማሪ ሃኪሞች ከሐምሊን አንጋፋ ሐኪሞች ከፍተኛ ልምድ የቀሰሙበት ዘመቻም እንደነበር ሪፖርቱ ያሳያል፡፡ በዘመቻው ከማህፀን መውጣት ህክምና በተጨማሪ በቅርቡ በተካሄደው የሩብ አመት ስራ አፈፃፀም ውይይት የተቀመጠውን አቅጣጫ መሰረት በማድረግ የመቀሌ ሐምሊን ፊስቱላ ማዕከልን የተከለሰ ማካካሻ ዕቅድንም ለመሸፈን መሞከሩን ዶ/ር መላኩ በሪፖርታቸው አስቀምጠዋል፡፡

የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ህክምናው ዘርፍ ዋና ኃላፊ ዶ/ር ፈቃደ በበኩላቸው ይህ አይነቱ ዘመቻ ከሃገሪቱ መንግስት ጋር ያለንን የቆየ የስራ ግንኙነት የበለጠ የሚያጠናክር ከመሆኑም ባሻገር የሐምሊን በዘርፉ ጥራት ያለው ውጤታማ ህክምና የመስጠት ልምድ እውቅናን የሚያገኝበትና ለሌሎች ባለሙያዎች የሚያካፍልበት በመሆኑ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል፡፡ ከስትራቴጂ አኳያም ባጠቃላይ በሃገሪቱ እናቶች ጤና ላይ ያለንን አስተዋፅኦ በተግባር ያሳየንበት እንደመሆኑ የስትራቴጂ ዕቅዳችን የትግበራ ምዕራፍ ተደርጎ የሚወሰድ ነው ብለዋል ዶ/ር ፈቃደ፡፡



# ሲስተር በሊ ቀሪ ዘመንሽ የተባረከ ይሁን!



የሐምሊንን ውሃ የቀመሰ እንዲሉ ቁጥራቸው በርከት ያለ የድርጅታችን ሠራተኞች ከትንሹ አስር እስከ ትልቁ አርባ ዓመታት በፍቅር ያገለገሉ እና እያገለገሉ የሚገኙ ናቸው፡፡ ገሚሶች በጡረታ ከተገለሉ በኋላም ተመልሰው በጊዜያዊ ሠራተኝነት ሲያገለግሉ ማየት የተለመደ ነው፡፡ ይህ ለምን ሆነ የሚል ካለ ብዕሩን አንግቦ ወረቀቱን ሰድሮ በማጥናት ተጨባጭ ምላሽ ማግኘት ይችላል፡፡ አንድ ጥናት የማይሻ እውነታ ግን አለ-መስራቾቹ ዶክተሮች ካትሪን እና ረጅናልድ የገነቡት መልካም የሠራተኞች እርስበርስ ግንኙነትና ጠንካራ ድርጅታዊ የስራ ባህል፡፡

ይህን ከመሰለ መልካም የእርስበርስ ግንኙነትና ጠንካራ የስራ ባህል ታዲያ አንድ ሠራተኛ በማንኛውም ሰበብ ሲለይ ሆዱን ባርባር ብሎት ማልቀስ የሚዳዳው ብዙ ነው፡፡ በቅርቡ በሚያዚያ ወር የሆነውም ይሄው ነው፡፡

ዘወትር ከሰኞ እስከ አርብ በሙሉ ነጭ የስራ ልብሷና ፈገግታ በማይለየው ተግባቢ ፊቷ ከትንሽ ትልቁ እየተጫወተች ግቢው ውስጥ ታካሚዎቿን ለማግኘት ከወዲያ ወዲህ ስተንቀሳቀስ ታሳልፋለች፡፡ ይህ እንቅስቃሴ በግቢ ውስጥ ለአንድ ቀን ሲጎል ሲስተር በሊ የለችም ማለት ነው፡፡ አሁን ግን ይህን ደማቅ እንቅስቃሴ በየቀኑ እንዳናየው ግድ የሆነ ይመስላል፡፡ በሐምሊን ብቻ ላለፉት 12 ዓመታት ያለድካም ካገለገለች

በኋላ በህጉ መሰረት የጡረታ ግዜዋ ደርሶ የጡረታ መብቷን አስከብራ ባሳለፍነው ሚያዚያ ወር በተዘጋጀ የመሰናበቻ ፕሮግራም አብዛኛው ሰራተኛ በተገኙበት በተቀላቀለ የሃዘንም የደስታም ስሜት ውስጥ ሆና በይፋ ተሰናብታለች፡፡ በእርግጥም ሐምሊንን ጨምሮ በተለያዩ ድርጅቶች ለ43 ዓመታት ካገለገሉ በኃላ ለጡረታ መብቃት አስደሳች የህይወት ምዕራፍ ነው፤ግን ደግሞ እንደ ሐምሊን ካለ መልካም የስራ ከባቢ መለየት ሲታሰብ ደግሞ ማዘን የማይቀር ይሆናል፡፡

ስሜታቸውን ለመግለፅ እድል አግኝተው የተናገሩት ሁሉ የሲ/ር በሊን መልካም ባህሪ እየጠቀሱ መለየታቸው አሳዛኝ ቢሆንም መልካም የእረፍት ዘመንን ተመኝተውላታል፡፡ እሷም በበኩሏ ከስራ ዘመኗ ሁሉ የሐምሊን ቆይታዋ አስደሳቹ እንደሆነና ስስት የሌለበት ፍቅርን ላሳዩዋት የሐምሊን ሠራተኞች በሙሉ ምስጋናዋን በማቅረብ ተሰናብታለች፡፡ ሐምሊን እንደ ሁለተኛ ቤቷ እንደመሆኑ እየመጣች እንደምትጎበኘን ሲ/ር በሊ ቃል ገብታለች፡፡

# የሐምሊን ምልክቶች...



ገበታቸው፣ ለአንዳንዶቹ የቤተሰብ ያህል ተቀራርበው በመተሳሰብ የሚኖሩበት ውሎ ማደሪያ ቤታቸው በመሆኑ ከድርጅቱ ጋር ያላቸው ቁርኝት ጠንካራና ረጅም ነው፡፡ የእነሱን የሐምሊን ቆይታ ለማስላት በቀላሉ መጀመሪያ ለህክምና የመጡበትን ወቅት ማወቅና

እነሱ በሐምሊን ሁሉም ናቸው፡፡ በሁሉም ዘርፍ ነርሶቻችንን ሲያግዙ ይውላሉ፤ታካሚዎችን የእናት ያህል ይንከባከባሉ፤ ማረፊያቸውን ሳይሰለቹ ያፀዳሉ፤ የታካሚዎችን የሰውነት ሙቀት እና የደም ግፊት በመሳሪያ ይለካሉ፤ አስተርጓሚም ይሆናሉ... ሌላም ሌላም፡፡ እነሱ በሐምሊን ሁሉም ቦታ አሉ፡፡ ዋርድ፣ ምርመራ ክፍል፣ቀዶ ጥገና ክፍል፣ ላቦራቶሪ፣ ስቶማ ክፍል፣ ፊዚዮ፣ ትምርት ክፍል፣ እጅ ሥራ ቦታ፣ ደስታ መንደር፣ ኮሌጅ፣ በአምስቱም የክልል ቅርንጫፎች.... ብቻ ምን አለፋችሁ የሌሉበት ቦታ የለም፡፡ እነሱ በየተሰማሩበት የስራ ዘርፍ የዕለት ተግባራቸው በከፍተኛ ፍላጎትና ባለቤትነት ስሜት ውስጥ ሆነው ሲያከናውኑ ላያቸው በወር ምንዳ የሚሰሩ አይመስሉም፡፡ ለእነሱ ሐምሊን ከፊስቱላ የዳኑበት መዳኛቸው፣ መተዳደሪያ ገቢ የሚያገኙበት የስራ

እስከአሁን መደዳውን መቁጠር በቂ ነው፡፡ ከእነሱ አንዳቸውም ከሐምሊን ውጪ ባለ ድርጅት ተቀጥረው ሰርተው አያቁም፡፡ ብዙዎች የሐምሊን የጀርባ አጥንት ናቸው ይሏቸዋል፡፡

ለአብዛኛዎቻችን ሠራተኞች ከላይ ያለው አንቀፅ ስለነማን እንደሆነ ለመረዳት ከሁለት መስመር በላይ ማንበብ አያስፈልገን ይሆናል፡፡ አዎ በትክክልም ስለነርስ ኤይዶች ነው፡፡ የእነሱ ልዩ መሆን የሚጀምረው ከስራ መደባቸው መጠሪያ ነው፡፡ በወፍ በረር በተደረገ የመረጃ ቅኝት እስካሁን በኢትዮጵያ ነርስ ኤይድ በሚል ስያሜ የሚታወቅ የስራ መደብ ከሐምሊን ውጭ በሌላ መሰል የመንግስትም ሆነ የግል ተቋም የለም፡፡ በትክክል ስለአጀማመሩ በፅሁፍ የተቀመጠ ማስረጃ ባይኖርም ከአንጋፋ የስራ ባልደረቦች መረዳት እንደተቻለው ነርስ ኤይድ እና ሐምሊን የተቋሙን እድሜ

ያህል ለአርባ አመታት የሚዘልቅ ታሪክ አላቸው፡፡ ያኔ ድርጅቱ በሰውሃይልም በአቅምም እንደአሁኑ ሳይደራጅ መስራቾቹ ዶክተሮች ካትሪን እና ሬጅ ሐምሊን ባጋጠማቸው ከባድ ጉዳት የተነሳ በአንድ ጊዜ ህክምና ያልዳኑና ተጨማሪ ህክምና እና ክትትል የሚፈልጉ ታካሚዎቻቸውን ወደ መጡበት ቢመልሷቸው ዳግመኛ አይመጡም በሚል ስጋት ለሳሙና በሚል ትንሽ ክፍያ እየሰጡ ህሙማኑን የመንከባከብና የጽዳት ስራ እንዲሰሩ እንዳደረጉዋቸው ይነገራል፡፡ በዚህ መልኩ የጀመረው ነርስ ኤይድነት ከሐምሊን ጋር ያስተሳሰረውን ቤተሰባዊ ቁርኝት ላለፉት አርባ በላይ አመታት ቀጥሎ አሁን ላይ በመላው ሐምሊን ፊስቱላ ማዕከላት ቁጥራቸው ከ150 የሚበልጡ ነርስ ኤይዶች የድርጅቱን የዕለት ተዕለት ተግባራት እያቀላጠፉ ይገኛሉ፡፡

የሐምሊን ነርስ ኤይዶች ከመደበኛ የየክፍሉ ስራቸው በተጨማሪ ለህክምና ለሚመጡ የፊስቱላ ታካሚዎች የምክርና መፅናናት አገልግሎት የሚሰጡ የስነ ልቦና ባለሙያዎችም ናቸው፡፡ ልብ በሉ የነሱ የምክር አገልግሎት በራሳቸው ላይ ከደረሰ የህይወት ተሞክሮ የሚነሳ በመሆኑ ታካሚዎቻችን ላይ የሚያሳድረው በጎ ተፅዕኖ ውጤታማ ነው፡፡ ድንገት እግር ጥሎት ወደ ቀዶ ጥገና ክፍል ለገባ ደግሞ ሃኪሞቹ፣ነርሶቹ እና ሌሎችም የክፍሉ ቡድን አባላት ታካሚዋን አልጋ ላይ አስተኝተው በትኩረትና በፀጥታ ለቀድመ ዝግጅት ከወዲያ ወዲህ ሲሉ አንድ በዕድሜ ጠና ያሉ ግን ደግሞ ንቁ የሆኑ ነርስ ኤይድ ታካሚዋን በቅርብ ሆነው በፍቅር ሲያጽናኗት ቋንቋዋን ባይችሉ እንኳን ለዚሁ ሲሉ ያጠኗቸውን ቃላት በመጠቀም ፊቷን እየደባበሱ አይዞሽ ሲሏት ማየት ስሜትን የሚነካና ሌላኛው የነርስ ኤይዶች ስነልቦናዊ ሚናን የሚያሳይ ነው፡፡ ሲስተር ጤናዳም፣ የድርጅቱ ሜትረን፣ ስለ ነርስ ኤይዶች እንዲህ ትላለች፣ “እነሱ የሐምሊን ምልክቶች ናቸው፡፡ አንዳንዶች እድሜያቸው ገፍቶ እንኳን ድካም አይታይባቸውም፡፡ ከቆይታ ብዛት ብዙውን ስራ የለመዱ በመሆናቸው ለነርሶቻችን ከፍተኛ እገዛ ያደርጋሉ፡፡”





የሐምሊን ዜና መጽሔት በሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ኮሚዩኒኬሽን ክፍል በየሦስት ወሩ እየተዘጋጀ ለድርጅቱ ሠራተኞች የሚሰራጭ ነው፡፡

አስተያየት ወይም ለዜና የሚሆኑ ሀሳቦች ካለዎት ያድርሱን፡፡

*ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ*
*ኮሚዩኒኬሽን ክፍል*
*ስልክ፡+251 113 720083*
*ፋክስ፡+251 113 726252*
*ኢሜይል፡enquiries@hamlinfistula.org*
*ዌብ ሳይት፡www.hamlinfistula.org*

Hamlin Fistula Ethiopia

*Designed & Printed by Everest Printers*